Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር Ref.No. 1.0/701
ቀን Date 05 የካቲት 2006

**በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ**

**<u>በያሉበት፣</u>**

**ጉዳዩ፡ <u>የአልባሳት አምራቾች የኤክሳይዝ ታክስ አከፋፈልን ይመለከታል፤</u>**

በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/1995 /እንደተሻሻለው/ እና ይህንኑ አዋጅ መሠረት በማድረግ በወጡ መመሪያዎች የተዘጋጁ ልብሶችን የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች የሚጠቀሙትን ግብዓት ከውጭ አገር ሲያስመጡም ሆነ ከአገር ውስጥ ግዥ ሲፈጽሙ የከፈሉት የኤክሳይዝ ታክስ ከሚያዝያ 3 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ በአልባሳቱ የማምረቻ ወጪ ላይ ሊከፍሉት ከሚገባው የኤክሳይዝ ታክስ ተቀናሽ እንዲደረግ ተፈቅዷል፡፡ ይሁንና ከውጭ ወደ አገር በሚገቡ ግብዓቶች ላይ የተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ መጠን በጉምሩክ ዲክላራሲዮን ላይ በግልፅ የሚታይ ቢሆንም በአገር ውስጥ በሚፈጸሙ የግብዓት ግዥዎች ላይ የተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ግን በግዥ ደረሰኙ ላይ በግልጽ የማይሰፍር በመሆኑ ታክስ የማቀናነስ ሂደቱ በህጉ መሠረት ተፈጻሚ ሳይደረግ ቆይቷል፡፡

ይህንን በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠመውን ችግር ለማቃለል የአልባሳት አምራቾች ዋንኛ ግብዓት የሆነውን ጨርቃ ጨርቅ ከአገር ውስጥ አቅራቢዎች ሲገዙ የሚከፍሉትን የኤክሳይዝ ታክስ መጠን በግዥ ደረሰኙ ላይ ከተጠቀሰው የሽያጭ ዋጋ በመነሳት ለማቀናነስ እንዲቻል በባለስልጣኑ የተዘጋጀው የሒሳብ ቀመር ተፈጻሚ እንዲሆን በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተቀባይነት ማግኘቱን ሚኒስቴሩ ጥር 19 ቀን 2006 ዓ/ም በቁጥር ጉ/መ/ኤ/ቀ/3/13 በጻፈው ደብዳቤ አስታውቋል፡፡ ስለሆነም በፋብሪካ ከጨርቃ ጨርቅ የሚሰሩ ወይም የሚዘጋጁ ልብሶች አገር ውስጥ ሲመረቱ ኤክሳይዝ ታክሱ ቀጥሎ በተመለከተው መሠረት እንዲከፈል ተወስኗል፡፡

1. የአልባሳት አምራቾች በግብዓት ላይ የከፈሉትን ኤክሳይዝ ታክስ ማቀናነስ እንዲችሉ በህግ ከተፈቀደበት ጊዜ ጀምሮ ታክሱ ስለሚቀናነስበት አግባብ ግልጽ የሆነ አሠራር ያልነበረ በመሆኑ አምራቾቹ ኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለበትን ግብዓት ዋጋ ሳያካትቱ፣ የኤክሳይዝ ታክስ በማስላት ይከፍሉ የነበረበት አሠራር ተቀባይነት ያገኘ ስለሆነ እስከ ጥር 30 ቀን 2006



ስልክ. / Tel. 011-466 74 66
ፋክስ / Fax 011-466 82 44
ኢሜል / E-mail erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website WWW.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ. / P.O.Box 2559
አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

ዓ/ም ድረስ ላለው ጊዜ ኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለበት ግብዓት ዋጋ በአልባሳቱ የማምረቻ ወጪ ሳይካተት በቀሪው የማምረቻ ወጪ ላይ የኤክሳይዝ ታክሱ ተሰልቶ እንዲከፈል እንዲደረግ፣

2. ከየካቲት 1 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ግን የአልባሳት አምራቾች በግብዓትነት በሚጠቀሙትን ጨርቃ ጨርቅ ከውጭ ወደ አገር ሲያስገቡ የተከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ መጠን ከጉምሩክ ዲክላራሲዮን ላይ፣ ከአገር ውስጥ ሲገዙ ደግሞ ከግዥ ደረሰኙ ላይ ከተመለከተው ዋጋ ውስጥ (የተጨማሪ እሴት ታክስን ሣይጨምር) 9% (ዘጠኝ በመቶ) በዚህ ግብዓት ላይ እንደተከፈለ የኤክሳይዝ ታክስ ተወስዶ በህግ በተፈቀደው መሠረት በወሩ ባመረቱት አልባሳት ላይ መከፈል ካለበት ኤክሳይዝ ታክስ በማቀናነስ ታክሱን በማስታወቅ የታክስ ግዴታቸውን እንዲወጡ እንዲደረግ፤

3. የአልባሳት አምራቾች በህግ የተፈቀደላቸው ታክስ የማቀናነስ መብት ከተፈቀደበት እና ይህ የአሰራር መመሪያ እስከተላለፈበት ጊዜ ድረስ የኤክሳይዝ ታክስ ተወስኖ የውሳኔ ማስታወቂያ የደረሳቸው ሆኖ፣ ክፍያ ሳይፈጽሙ ጉዳያቸው በተለያየ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የታክሱ ከፋዮች የተሰጠ የኤክሳይዝ ታክስ ውሳኔ በተራ ቁጥር 1 ላይ በተመለከተው መሠረት ተስተካክሎ እንዲወሰን እና በዚህ መሠረት ያልተከፈለ ቀሪ ታክስ ካለ እንዲከፈል እንዲደረግ፤

4. የአልባሳት አምራቾች የግብዓት ኤክሳይዝ ታክስ ተቀናሽ/ተመላሽ የሚደረግላቸው በመሆኑ ከላይ በተራ ቁጥር 2 ከተገለጸው ጊዜ ጀምሮ በግብዓት ላይ የከፈሉት የኤክሳይዝ ታክስ በተሰብሳቢ ሂሳብ (Receivable) መመዝገብ እንዳለበት እና በግብዓቱ የግዥ ዋጋ (Cost) ላይም መካተት እንደሌለበት ወይም ከግዥ ዋጋ /Cost/ ላይ ተቀናሽ መደረግ እንዳለበት እንዲገለጽላቸው፣

በመሆኑም በፋብሪካ ከጨርቃ ጨርቅ የሚሰሩ ወይም የሚዘጋጁ ልብሶች የሚያመርቱ የታክሱ ከፋዮች የግብአት ግዥ ላይ የከፈሉት የኤክሳይዝ ታክስ ተቀናሽ ከላይ በተገለጸው መሠረት እንዲፈጸም የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎችና ሠራተኞች እንዲያውቁትና በዚሁ መሠረት ስለመፈጸሙም ተገቢው ክትትልና ድጋፍ እንዲደረግ እያስታወቅን፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተጻፈውን ደብዳቤ ኮፒ 1 ገጽ አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት አምራቾች ማህበርም አባላቱ ውሳኔውን አውቀው በዚሁ መሠረት የታክስ ግዴታቸውን እንዲወጡ ለአባላቱ እንዲያሳውቅ የዚህ ደብዳቤ ግልባጭ እንዲደርሰው ተደርጓል፡፡

ከሰላምታ ጋር

በከር ሻሌ ዱሌ
ዋና ዳይሬክተር

አባሪ 1 ገጽ

ግልባጭ፣

- ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
- ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
- ለኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት አምራቾች ማህበር

  አዲስ አበባ፣

- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለኦፕሬሽን ፕሮግራም ዲዛይንና ልማት ሥራዎች ዘርፍ
- ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ማስተባበሪያና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለሕግ ማስከበር ሥራዎች ዘርፍ
- ለለውጥና ሞደርናይዜሽን ሥራዎች ዘርፍ
- ለግብር አወሳሰንና አሰባሰብ አሠራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ኦዲት አሠራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለአገር ውስጥ ታክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለክልሎች ድጋፍና ትብብር ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለኢንቨስትመንት ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለዐቃቤ ህግ ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት
- ለትምህርትና ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

  የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

- ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለምሥራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- ለሐዋሣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- ለባሕርዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- ለመቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- ለጅማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- የአዲስ አበባ ቁጥር 1 መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- የአዲስ አበባ ቁጥር 2 መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለቦሌ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለአራዳ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለጉለሌ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለቂርቆስ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለየካ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለልደታ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለመርካቶ ቁጥር 1 ቅ/ጽ/ቤት
- ለመርካቶ ቁጥር 2 ቅ/ጽ/ቤት

<u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን</u>

- ለትግራይ ክልል የገቢዎች ልማት ባለስልጣን /መቀሌ/
- ለአፋር ክልል ገቢዎች ባለስልጣን /ሰመራ/
- ለአማራ ክልል ገቢዎች ባለስልጣን /ባህር ዳር/
- ለኦሮሚያ ክልል ገቢዎች ባለስልጣን /አዲስ አበባ/
- ለሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ /ጅጅጋ/
- ለቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል ገቢዎች ባለስልጣን /አሶሳ/
- ለደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል ገቢዎች ባለስልጣን /ሀዋሳ/
- ለጋምቤላ ክልል ገቢዎች አስተዳደር ባለስልጣን /ጋምቤላ/
- ለሐረሪ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለስልጣን /ሐረሪ/
- ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ኤጀንሲ /ድሬዳዋ/

PDF Complete
Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

ፌናፈ
22/5/06
10:15

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Development

ቁጥር ጉ/ጠ/ኬ/ቀ/3/13
Ref. No

ቀን 19 ጥር 2006
Date

0121667
23/05/06

ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

<u>አዲስ አበባ</u>

በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ማሻሻያ እና ይህንኑ አዋጅ መሠረት በማድረግ በወጡ መመሪያዎች የአልባሳት አምራቾች በግብዓትነት የሚጠቀሙበትን ጨርቅ ከውጭ አገር ሲያስመጡም ሆነ አገር ውስጥ ሲገዙ የከፈሉትን የኤክሳይዝ ታክስ አልባሳቱን ሲያመርቱ በማምረቻ ወጪው ሊከፍሉት ከሚገባው የኤክሳይዝ ታክስ ጋር እንዲያቀናንሱ የተፈቀደ ቢሆንም ለኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ መሠረት የሆነው የማምረቻ ወጪ በኢንቮይስ ላይ በግልጽ ስለማይመለከት ታክሱን ለማቀናነስ ያልተቻለ መሆኑን በመግለጽ፣ ይህንን ችግር ለማቃለል የተዘጋጀውና በአልባሳት አምራቾች ማህበር ተቀባይነት ባገኘው የመፍትሔ ሃሳብ ላይ ስምምነታችንን እንድንገልጽ በ23/4/2006 በቁጥር 1.0/671/23 በተጻፈ ደብዳቤ የተጠየቀውን ይመለከታል።

የቀረበው የመፍትሔ ሃሳብ በመ/ቤታችን ከተመረመረ በኋላ ተቀባይነት አግኝቷል። ስለዚህ ፦

1. የአልባሳት አምራቾች በግብዓት ላይ የከፈሉትን ኤክሳይዝ ታክስ ማቀናነስ እንዲችሉ በሕግ ከተፈቀደበት ጊዜ ጀምሮ ይህ መመሪያ እስከተላለፈበት ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ታክሱ ስለሚቀናነስበት አግባብ ግልፅ የሆነ መመሪያ ያልነበረ በመሆኑ በተለምዶ ሲሰራበት በነበረው ዓይነት ከአልባሳት የማምረቻ ወጪ ላይ ኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለበት ግብዓት ዋጋ ተቀንሶ በቀሪው ሂሳብ ላይ የኤክሳይዝ ታክሱ ተሰልቶ እንዲከፈል፣

2. ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የአልባሳት አምራቾች በግብዓትነት የሚጠቀሙበትን ጨርቃጨርቅ ግዥ ሲፈጽሙ ከተከፈለው ዋጋ ውስጥ (የተጨማሪ እሴት ታክስን ሳይጨምር) 9% በዚህ ግብዓት ላይ እንደተከፈለ የኤክሳይዝ ታክስ ተወስዶ በህግ በተፈቀደው መሠረት ባመረቱት አልባሳት ላይ መከፈል ካለበት ኤክሳይዝ ታክስ በማቀናነስ የታክስ ግዴታቸውን እንዲወጡ እንዲደረግ በቀረበው ሃሳብ መስማማታችንን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

ሱፍያን አህመድ
ሚኒስትር

ግልባጭ፣
- ለማክሮ ኢኮኖሚ ማኔጅመንትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- <u>ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር</u>

Lett.W/GT

ስልክ
TEL 251-11-155 24 00, 22 66 98
251-11-155 00 81, 83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905, 1037
ፋክስ
FAX. 251-11-155 13 55, 55 14 96
251-11-155 38 44
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
Addis Ababa - Ethiopia

PDF Complete
Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features